# አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን

# የዛፍ መቁረጥና ማዘዋወር ፈቃድ አሰጣጥ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 01/2012

ሰኔ/2012 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

**መግቢያ**

ዛፍ/ዛፎች/ለህብረተሰቡ የሚሰጡት ጥቅም ከፍተኛ በመሆኑና ይህንን ጥቅም ቀጣይነት እንዲኖረዉ የዛፍ ባለቤት መብት ሊጠበቅ ሆኖ ለከተማው ህብረተሰብ ከሚሰጡት ዘርፈ ብዙ ጥቅምና አገልግሎት አኳያ ዛፍ ለመቁረጥ ወይም ለማዘዋወር ህጋዊ አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ከዛፍ/ዛፎች የሚገኘዉን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጠቀሜታ ዘላቂ ለማደረግ እና በዘፈቀደ የመቁረጥ ባህልን በማስቀረት በህጋዊ መንገድ ተቆረጦ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል የአጠቃቀም ስርአት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ዛፍ/ዛፎች /ከፍተኛ አገልግሎት ያላቸዉ ቢሆንም በአግባቡና በወቅቱ ጥቅም ላይ ካልዋሉ በከተማዉ በሚገኙ ት መሰረት -ልማቶችና የመኖሪያ አካባቢዎች እንዲሁም በሰዉ ህይወትና ንብረት ላይ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ይህንን ከግምት ዉስጥ በማስገባት የዛፍ /ዛፎችን/ ለመጠቀመ እንዲቻል ህጋዊ መሰረት እንዲኖረዉ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 11 መሰረት ከፈቃድ ሰጪዉ ኮሚሽን መሰሪያቤትና እና ከኮሚሽኑ ተጠሪ መሰሪያቤቶች ፍቃደ ሳያገኙ በግልምሆነ በማህበር የለሙትን ዛፎች እንዳይቆርጡ/እንዳያዘዋዉሩ /ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን ተዘጋጅቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አከባቢ ጥበቃና አሪንጓዴ ልማት ኮሚሽን የዛፎ/ዛፎች/ማዘወርና መቁረጥ ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ ተብሎ ሊጠቀሰይችላል፤

2. **ትርጓሜ**

ቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠዉ ካልሆነ በሰተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ ፡-

1.‹‹**ዛፍ**›› ማለት በዓይነት፤ ኮሚሽኑ ዛፍ ብሎ የሚሰይመዉና በመጠኑ ሳይለይ የእንጨትነት ፀባይ ያለዉ ተክል ነዉ፡፡

2.‹‹**ዛፍ መቁረጥ** ›› ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ዛሮችን ከነበሩበት ቦታ ላይ በመቁሪጥ ማንሰት ማለት ነዉ፡፡

3.‹‹**የዛፍ ማዘዋወር** ›› ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ዛፎችን በቋሚነት ያድጉ ከነበረበት ቦታ ወደሌላ ሲያድጉ ወደሚችሉበት ቦታ ማዘዋወር ማለት ነዉ፡፡

5.‹‹**የዛፍ ማዘዋወሪያ ጥያቄ ማሰተናገድ** ›› ማለት ግለሰቦች /ድርጅቶች ማህበራት በግል ይዞታቸው የሚገኙትን ዛፎችን ለማዘዋወር ሲፈልጉ በቅድሚያ ለኮሚሽኑ ለክ/ከተማ ወይም ለወረዳዉ አካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ፅ/ቤት ማዘዋወር ፈቃድ እዲያገኙ ጥያቄ በማቅረብ የሚሰተናገዱበት አሰራር ነዉ፡፡

6.‹‹**የፊቃድ ሰጪዉ መ/ቤት** ›› ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር አካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን እና ተጠሪ ነታቸዉ ለኮሚሽን መሰሪያቤቱ የሆኑት ከክ/ከተማ እሰከ ወረዳ ያለዉ መዋቅር ማለት ነዉ፡፡

7.‹‹**ፈቃድ**›› ማለት በዚህ መመሪያ መስረት የለማ ዛፍ ለማዛወር፣ ለመቁረጥ እና ለመጠቀም የተሰጠ ፊቃድ ማለት ነዉ ፡፡

8.‹‹**የፈቃድ ክልል**›› ማለት ማናችዉም ፈቃድ የተሰጠበት ሰፍራ ነዉ፡፡

9.‹‹**ሮያሊቲ ክፍያ**›› ማለት በመንግሰት ሆነ በግል የለሙ ዛፎችን ለመቁረጥ ፈቃድ ለወሰደ ባለ ፈቃድ ከሚቆረጡት ዛፍ/ዛፎች /ላይ ዉጤቱ በመቶ እየተሰላ የሚከፈል ክፍያ

**3. የተፈፃሚንት ወሰን**

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር ክልል ዉሰጥ ዛፍ በሚገኝባችዉ ቦታዎች ይዞታ እና ክልል ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**4. የመመሪያ ዓላማ**

በአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር ክልል ዉሰጥ የሚገኙትን ዛፍ/ዛፎችን/ ለመቁረጥ ለማዘዋወር እንዲቻል የፈቃድ አሰጣጥና ፈቃድ ጠያቂዎች

ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለዉ አሰራር ለመዘርጋት፤

**5 የፈቃድ ሰጭዉ አካል ተግባርና ኃላፊነት**

**5.1 ፈቃድ ሰጭዉ መ/ቤት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡**

ሀ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ፈቃድ የሚያሰጡ ሁኔታዎች መኖራቸዉን ያረጋግጣል፤

ለ በከተማ፣ ክ/ከተማ እና ወረዳ የቀረበዉን ጥያቄ በባለሙያዎች ያስጠናል፤

ሐ የቀረበዉ የጥናት ሪፖርት ገምግሞ/መርምሮ/ ፈቃድ ለመስጠት በቂሆኖ ካገኘው ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ያረጋግጣል፤

መ ፈቃድ ጠያቂዉ ፈቃድ በጠየቀበት ዛፍ ላይ ህጋዊ ባለቤትን ወይም በህግ የተሰጠ የባለቤትነት መብት እንዳለዉ ያረጋግጣል፤

ሠ ፈቃድ የተሰጠዉ አካል ቆረጣ ከማካሄዱ በፊት የሮያሊቲ ክፍያ እዲከፍል ያደርጋል፡፡

ረ አገልግሎት ጠያቂዉ የሚጠበቅበትን ሁሉ ማሟላቱ ሲረጋገጥ ዛፉን/ዛፎችን/ የመቁረጥና የማዛዋወር ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

**6. የሕግ ማዕቀፎችና አሰተዳደራዊ መዋቅሮች**

በዚህ መመሪያ ዉስጥ የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች ለመሰጠትም ሆነ ክፍያዎችን ለማሰከፈል መነሻ የሆኑ የሕግ ማዕቀፎችና አሰተዳደራዊ መዋቅሮች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

- በፌደራል መንግሰት የጸደቁ አዋጆችና ደንቦች
- የፌደራልና የክልል አካላት ተግባር ለመወሰን የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 41/1985
- የደን ልማት፤ጥበቃና አጠቃቀም /አዋጅ ቁጥር 1065/2010
- የአዲሰ አበባ ከተማ አሰተዳደር የአሰፈጻሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 64/2011

**7 የፈቃድ ተቀባይ (ጠያቂው አካል) ተግባርና ኃላፊነት**

***የዛፍ/የዛፎች/ ባለቤት*** ማለት ዛፍ /ዛፎችን/ በራሱ ይዞታ ወይም ለመጠቀም በህግ (ኪራይ ወይም ሰጦታ) በተሰጠዉ ቦታ ላይ ያለማዉ ግለሰብ፣ ድርጅቶች፣ ማህበራት፣ መንግሰታዊ ወይም መንግሰታዊ ያልሆነ ደርጅቶች/ተቋማት/ ማለት ነዉ፡፡

ሀ. ጥያቄዉን በፅሑፍ ማቅረብ አለበት፤

ለ. ህጋዊ የይዞታ ማሰረጃ ማቅረብ አለበት ፤

ሐ. የዛፎቹን አይነትና ቁጥር መግለጽ አለበት፤

መ. የሚያዘዋወርበትን ወይም የሚቆርጥበትን ምክንያት እና ማሰረጃ ማቅረብ አለበት፤

ሠ. ሊቆረጥ የታሰበዉ ዛፍ በሁለት ግለሰቦች ወይም ደርጅቶች አዋሳኝ ከሆነ በጋራ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፤

ረ. የሁለቱም ወገን ስምምነት ከሌለ የፍ/ቤት ውሳኔ ኮፒ አያይዞ ማቅረብ አለበት፤

ሸ. ለኃይማኖት ተቋማት፣ ብዙሀን ማህበራትና መንግሰታዊ የልሆኑ ድርጅቶችን በተመለከት የመቁረጥ ፍቃድ ጥያቄ ደብዳቤ እና ከሚመለከተዉ አካል የተጻፈ ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብዳቤ መቅረብ አለበት፤

ቀ. ማንኛዉም መንግስታዊናመንግስታዊ የልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ግለሰቦች ዛፍ ለማዛዋወርና ለመቁረጥ የሚያቀርቡት የፍቃድ ጥያቄ ደብዳቤዉ /ማመልከቻዉ ወጪ የሆነበት ጊዜ ከአንድ ወር ያልበለጠ መሆን ይገባዋል፡፡

በ. ማንኛዉም ዛፍ/ዛፎች/የመቁረጥም ሆነ የማዘዋወር ፈቃድ ከተፈቀደ በአንድ ወር ጊዜ ዉሰጥ ተግባራዊ መሆን አለበት፤

**8. የዛፍ መቁረጥና የማዛዋወር ፈቃድ ለመሰጠ ቅድሚያ ሊወሰዱ የሚገባችዉ ቅድመ ሁኔታዎች**

- ***የሚቆረጠዉ ዛፍ፡-***

ሀ. በጠያቂዉ ይዞታ ዉሰጥ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፤

ለ. እንዲቆረጥ ጥያቄ የቀረበበት ዛፍ በንብረትና በሰዉ ህይወት ላይ አደጋ የሚያስከትል መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሐ. የግንብና ቦይ መሰነጣጠቅ የሚያስከትል መሆኑ ሲረጋገጥ፤

መ. ከአቀማመጥ የተነሳ በድንገተኛ አዉሎ ነፋስ ኃይል ተገፈቶ ቢወድቅ በሚከተሉት ላይ አደጋ እንደሚያስከትል ከተረጋገጠ፡

- በሰዉ መኖሪያ ሕንፃ ቤት ፤
- በንግድ ቤቶች ፤
- በመንግሰትና የግል መሥሪያ ቤቶች ፤
- በሌሎች ንብረቶችና ሃብቶች ላይ፤
- ከመሬት በላይና በታች ባሉ የመንግሰት የመሰረተ ልማት አዉታሮች ላይ
- የህዝብና የግል መሰረት ልማት ተቋማቶች ላይ አደጋ እንደሚያስከትል ሲረጋገይ ፤
- በወሳኝ፤ አሰፈላጊ እና አንገብጋቢ የመንግሰት እና የግል ፕሮጀክቶች ምክንያት ዛፎችን ማዘዋወር ወይም መቁረጥ አሰፈላጊ ነዉ ብሎ ኮሚሽኑ ሲያረጋግጥ፤
- በእድሜ መግፈት ወይም በበሽታ ምክንያት እድገቱ ሲገታ ወይም መድረቁ በኮሚሽኑ ሲረጋገጥ፤
- በወንዝ ዳርቻ የዉሃ ጥራት ፍሰት የሚቀንሱ ሰለመሆናቸዉ ሲረጋገጥ፤
- ጥቅም ላይ ለመዋል መድረሱ ሲረጋገጥ፤

ሠ. የዛፉ የዕድሜ ደረጃ አገልግሎት ላይ ሊዉል የሚችልበት የዕድገት ደረጃ ላይ ሲደርሰ፤

ረ. ዛፉ የዕድገት ደረጃዉን ጨርሶ ሲያረጅ፤

ሰ. የዛፍ የዕድሜ ደረጃዉ አገልግሎት ላይ ሲዉል የሚችልበት የዕድገት ደረጃ ላይ የደረሰ ዛፍ ሲቆረጥ ቆራጩ በምትኩ ሌሎች ተመሳሳይ ችግኞችን መትከል አለበት፤

ሸ. በዛፍ ቆረጣዉ ወይም ማዘዋወር ወቅት በመሠረተ ልማት ላይ ሚደርሰዉን ጉዳት መልሶ በማልማት የማሰተካከል ግዴታ አለበት፤

## 9. የዛፍ መቁረጥ እና ለማዘዋወር ፈቃድ የሚሰጥባችዉ መሰፈርቶች

ሀ. ቁጥራቸዉ ከ1-50 የሚደርሱ ዛፎችን ለማዘዋወርና ለመቁረጥ የፈቃድ ጥያቄዉ የሚቀርበዉ ለወረዳ አካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ፅ/ቤት ሆኖ መልሱም እዚያዉ ይሰጣል፡፡

ለ. ቁጥራቸዉ ከ51-100 የሚደርሱ ዛፎችን ለማዘዋወርና የመቁርጥ ፈቃድ ጥያቄ ለክፍል ከተማዉ አካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ፅ/ቤት ሆኖ መልሱም እዚያዉ የሚሰጥ የሆናል፡፡

ሐ. ቁጥራቸዉ ከ100 በላይ የሚሆኑ ዛፎችን የማዘዋወርና የመቁረጥ ፍቃድ ጥያቄ የሚቀርበዉም ሆነ የሚሰጠዉ በአዲሰ አበባ ከተማ አሰተዳደር አካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ኮሚሽን ዋናዉ መ/ቤት ብቻ ይሆናል፡፡

**ክፍል ሁለት**

1. የመመሪያዉ አሰፈላጊነት

ሀ. ሚዛኑን የተጠበቀ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ሰርዓትን በማሰፈን ከዘርፉ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ለማመንጨት ማሰቻል፤

ለ. የዛፎችን ማዘዋወር፣ መቁረጥ እና ተያያዥ ጉዳዮችን ወጥ በሆነ መልኩ ለማሰተዳደር

ሐ. ዛፎች በእድሜ መግፋት ወይም ባልተጋባ አሰተዳደግ ወይም በአሰገዳጅ የልማት ፕሮጀክቶች ወይም በሰዉ ህይወት ፤ በመሰረተ ልማት ፤በንብረት ላይ አደጋ ያሰከትላል ተብሎ በታመነ ጊዜ በጥንቃቄ ለማሰወገድ ወይም ለማዛወር የሚያሰችል ወጥ አሰራር በማሰፈለጉ፡፡

## 2. <u>የዛፍ መቁረጥ እና ማዛወሪያ ጥያቄ ማሰተናገድ</u>

- አገልግሎቱ የሚወሰደዉ ጊዜ

| ተ/ቁ | ዝርዝር | | ጊዜ (ሰዓት) | ምርመፋ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ለዛፍ/ዛፎቹ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብዳቤ ባለጉዳዩ እንዳቀረበ ቀጠሮ ይወሰዳል፤ | | 1 | ይህ ሰሌት የሚሰራዉ ለአንድ ሄ/ር በታች ለሆነ የደን ሲሆን ከዚያ በላይ ከሆነ እንደ ቦታዉ ተደሪሽነትና አሰቸጋሪነት የሚወሰን ይሆናል፤ |
| 2 | በቀጠሮ አለት ባለሙያ መሰክ ላይ ጥናት ያደርጋል፤ | | 7 | |
| | የቢሮ ሰራ | | 7 | |
| 3 | 3.1 | ከመስክ በተሰበሰበዉ መረጃ መሰረት የዛፋን/ዛፎቹን ይዘት ማሰላትና የልማት ክፍያ መወሰን፤ | 5 | |
| | 3.2 | በጥናቱ መሰረት ባለጉዳዩ ክፍያዉን እንዲፈፅምና የመቁረጥ ፈቃድ እንዲወሰድ ማደረግ፤ | 2 | |
| | ጠቅላላ ጊዜ | | 15 | |

- **አሰራሩ/መመሪያው/ የሚመለከታቸዉ አካላት**

1. ማንኛዉም በአረንጓዴ ክልል ዉሰጥ የሚገኙ መንግሰታዊ፣ መንግሰታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ግለሰቦች እና ማህበራት

2. ከአረንጓዴናክልል ካርታ ዉጪ ያሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች

3. ትምህርትቤቶች

4. የሀይማኖት ተቋማት፣ ህዝባዊና መንግሰታዊ ድርጅቶች

5. የብዙሀኑ ማህበራት . . .ወዘተ

## 3. የባለጉዳይ መሰተንግዶ

ሀ. ደብዳቤዉ ለኮሚሽኑ፣ ለክፍለ ከተማ ወይም ለወረዳ አካባቢ ጥበቃና አረንጓዴ ልማት ፅ/ቤት በደረሰ ቀን በእለቱ ለባለጉዳዩ ቀጠሮ ይሰጠዋል፡፡

ለ. በቀጠሮዉ ቀን ባለሙያ ዛፉ በሚገኝበት ቦታ በመገኘት የቴክኒክ ጥናት ያካሂዳል፡፡

ሐ. ጥናቱ የሚወሰደዉ ጊዜ እንደ ዛፎቹ ብዛት ይወሰናል፡፡ ይኸዉም የጥናቱ ቦታ ከአንድ ሄክታር በታች ከሆነ ጥናቱ በአንድ ቀን ይጠናቀቃል፤

መ. ጥናቱ/መረጃዉ ከተሰበሰበ በኃላ መረጃዉን በማጠናከርና ሂሰቡን በማሰለት የሮያሊቲ ክፍያ ማሰከፈልና የፈቃድ ደብዳቤ አዘጋጅቶ ለባለጉዳይ ለመሰጠት በአንድ ቀን ይጠናቀቃል፤

4. የሮያሊቲ ክፍያ አከፋፈል

የሮያሊቲ ክፍያ ዓላማ መንግሰት ክክፍያዉ በሚሰበሰበዉ ገንዘብ በተለያዩ መንገዶች የአረንጓዴ ልማቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ ነዉ፡፡

በመሆኑም መንግሰት ለአረንጓዴ የልማት ሰራ ግብዓቶችና የደን ሰርዓተ ምህዳር መሰተጋብር ተጠብቆ ጠቀሜታ እንዲሰጥ ለማድረግ የሚያወጣችዉን ልዩ ልዩ ወጪዎች ግምት ዉሰጥ በማሰገባት ቀድሞ ሲከፈል ሲከፈል በነበረዉ ላይ መጠነኛ ማሰተካከያ ተደርጎ ክፍያዉ ክፍያዉ ቀጥሎ በተመለከተዉ አግባብ እንዲፈፀም ተወሰኗል፡፡

የዛፍ መቁረጥ እና የዛፍ ማዘዋወር የሮያሊቲ ክፍያ ሰንጠረዥ

***ሰንጠረዥ አንድ***

የዛፍ መቁረጥ ሮያሊቲ ክፍያ ሰሌት

| የዛፍ ዝርያ | የሮያሊቲ ክፍያ ሰሌት |
|---|---|
| የዉጪ የዛፍ ዝርያ (ባህር ዛፍ፣ ግራቪሊያ፣ ሳሊግና፣ ኦሜድላ፣ ሸዉሸዌ. . . ወዘተ) | ከመቶ ሀያ (20%) |
| አገር በቀል የዛፍ ዝርያዎች (ኮሶ፣ ወይራ፣ የአበሻ ጥድ፣ ብርብራ፣ ዝግባ፣ የአበሻ ግራር... ወዘተ | ከመቶ ሰላሳ(30%) |

## *ሰንጠረዥ ሁለት*

**የዛፍ ማዘዋወር ሮያሊቲ ክፍያ ሰሌት**

መነሻዎች ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ዉጭ ወደሌሎች የሀገሪቱ ክልሎች በታመነባችዉ ምክንያቶች የዛፍ ማዘዋወር ሰራ በሚከናወንበት ጊዜ እንዲሁም ከህዝብ መገልገያ ሰፍራዎች ወደ ማህበራት ወይም ድርጅቶች ወይም በታመነባችዉ የግል ፕሮጀክቶች ይዞታ በሚዘዋወሩበት ጊዜ፤

| የዛፍ ዝርያ | | የሮያሊቲ ክፍያ |
|---|---|---|
| የሀገር ውሰጥ መለሰተኛ ታዳጊ ዛፎች | ከሶሰት አሰከ አምሳት አመት ዕድሜ | 10 ሺ ብር |
| | ከአምሰት አመት በላይ | 20 ሺ ብር |
| የውጭ ሀገር መለሰተኛ ታዳጊ ዛፎች | ከሰድሰት ወር በላይ ዕድሜ ለሆናቸው | 2000 ሺ ብር |

**ክፍል ሶሰት**

1. **የተከለከሉ ድርጊቶች (ተግባራቶች)**

**ሀ.** ማንኛዉም ሰዉ ባለይዞታዉን ጨምሮ በኮሚሽኑና በሥሩ በሚገኙ የመዋቅር እርከኖች ሁኔታዉ ተጠንቶ እና ተረጋግጦ ከሚሰጠዉ ፈቃድ ውጪ ዛፎችን መቁረጥ አይችልም፤

**ለ.** ማንኛውም ባለይዞታ ራሱ ተክሎ ያለማቸውን በማጥፋት ላይ የሚገኝ የዛፍ ዝርያያዎችን በኮሚሽኑና ከሥሩ በሚገኙ የአሰተዳደር መዋቅሮች ተረጋግጦ ፈቃድ ሣያገኝ መቁረጥ አይችልም፤

2. **ቅጣት**

በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1065/2018 ላይ በተደነገገው መሰረት በዚህ መመሪያ ላይ የተጠቀሱትን የተከለከሉ ድርጊቶች ተላልፎ የተገኘ ማንኛዉም ሰዉ የደን ዉጤቱ መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአንድ አመት በማያንሰና ከአመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከአሰር ሺህ እሰከ ሃያ ሺህ ብር በሚደርሰ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3. **ተፈፃሚነት የሌላችዉ ህጎች**

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛዉም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ላይ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈጻሚነትአይኖረዉም፡፡

4. **መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ የአፈፃጸም መመሪያ በልዩ ሁኔታ በኮሚሽን መሰረያ ቤቱ ታይቶ ከጸደቀበት ከሰኔ 18 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡